https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፱
አዲስ አበባ የካቲት ፭ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 29
ADDIS ABABA 8th, February 2019,

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፩ /፪ሺ፲፭ ዓ.ም

የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ.....ገፅ ፲ሺ፱፻፺፪

CONTENT

Proclamation No. 1101 /2019

Administrative Boundary and Identity Issues Commission Establishment Proclamation.....page 10992

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፩ /፪ሺ፲፭
የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽንን ለማቋቋም
የወጣ አዋጅ

የፌደራል ስርዓቱን በማጠናከር እየተገነባ የመጣውን የብሔር ብሔረሰብ እና ህዝብ ብዝሃነት ማጎልበት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክልሎች የአስተዳደር ወሰን፣ ራስን በራስ ማስተዳደርና በማንነት ጥያቄዎች ዙሪያ በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮችን አገራዊ በሆነና በማያዳግም መንገድ መፍታት በማስፈለጉ፤

ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ውዝግቦች በተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መካከል የቅራኔ ምንጭ መሆናቸውን በመገንዘብ፤

ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ግጭቶች ከፍተኛ ለሆነ አለመረጋጋት መንስዔ በመሆናቸው፤ ለእነዚህ ችግሮች ገለልተኛ በሆነ፣ ከፍተኛ ሙያዊ ብቃት ባለውና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ማፈላለግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

PROCLAMATION No. 1101 /2019
A PROCLAMATION TO ESTABLISH ADMINISTRATIVE BOUNDARY AND IDENTITY ISSUES COMMISSION

WHEREAS, It is found necessary, by strengthening the Federal System to reinforce the underway diversity of Nations, Nationalities and Peoples;

WHEREAS, it is become necessary to solve issues of Administrative Boundary, Self-government and Identity questions that repeatedly occur in regions nationally and for lasting;

WHEREAS, it is realized that controversy relating Administrative Boundary is source of conflicts between various Nations, Nationalities and Peoples;

WHEREAS, it is becomes necessary the need for a neutral, highly professional and peaceful solution to these problems since conflicts with Administrative Boundary are a cause of great instability;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፩ /፪ሺ፲፩ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

፩/ "የአስተዳደር ወሰን" ማለት ራስን በራስ ማስተዳደር፣ ከማንነት ጥያቄ፣ከአስተዳደር ወሰን አከላለል እና ከሌሎች ተመሳሳይ ሁኔታዎች ጋር በተያይዘ የሚነሱ የወሰን ጉዳዮች ናቸው።

፪/ "ኮሚሽን" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፫(፩) መሰረት የተቋቋመ የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጥያቄ ጉዳዮች ኮሚሽን ነው።

፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፫. መቋቋም

፩/ የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ 'ኮሚሽን' እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ ኮሚሽኑ የአስተዳደር ወሰን፣ ራስን በራስ ማስተዳደር እና ማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን፣ ጽህፈት ቤት እና አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል።

፫/ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

፬. የኮሚሽኑ ዓላማ

ኮሚሽኑ አሳታፊ፣ ግልፅ፣ አካታችና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከአስተዳደር ወሰኖች፣ ራስን በራስ ማስተዳደር እና ከማንነት ጋር የተያይዙ ግጭቶችንና መንስኤያቸውን በመተንተን የመፍትሄ ሃሳቦችን ለህዝብ፣ ለፌደሬሽን ምክር ቤት፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለአስፈጻሚው አካል ማቅረብ ነው።

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Administrative Boundary And Identity Issues Commission Establishment Proclamation No.1101 /2019."

2. Definition

1/ "Administrative Boundary" means issues related to Self-Administration, identity questions, Administrative Boundary Demarcation and other similar events that rise in relation to Boundary issues.

2/ "Commission" means 'Administrative Boundaries and Identity issues Commission' established under Article 3 (1) of this Proclamation.

3/ "Person" means any physical or juridical person.

3. Establishment

1/ Administrative Boundary Commission (hereinafter referred to as "The Commission") is hereby established by this Proclamation.

2/ The Commission shall have Administrative Boundary and Identity Question Commission, its Own Office and Necessary Staff.

3/ The Commission shall be accountable to the Prime Minister.

4. Objectives of the Commission

The objectives of the commission shall be to submit recommendation to the Public, the House of Federation, the House Of People's Representatives and the Executive Organ through analysis of causes and conflicts arises in relation to Administrative Boundaries, self-government and identity issues in participatory, explicit, inclusive and scientific manner.

https://chilot.me

፭. <u>የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባራት</u>

በህገመንግስቱና በሌሎች ህጎች ለፌደሬሽን ምክር ቤት እና ለክልሎች የተሰጠ ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ከአስተዳደራዊ ወሰኖች አከላለል፣ ራስን በራስ ማስተዳደር እንዲሁም ከማንነት ጥያቄ ጋር የተገናኙ ማናቸውንም ችግሮችንና ግጭቶችን በጥናት ለይቶ አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤

፪/ በህዝቦች እኩልነትና ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ስር እንዲሰድና እንዲዳብር ለማድረግ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ማሻሻያ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ምክረ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

፫/ አስተዳደራዊ ወሰኖች በቀጣይነት የሚወሰኑበትንና የሚለወጡበትን መንገድ በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን ህገ መንግስታዊ መርሆዎች ያገናዘበ፣ ግልጽና ቀልጣፋ ሥርዓት ወይም የህግ ማሻሻያ እንዲዘረጋ ጥናት በማድረግ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለፌደሬሽን ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤

፬/ ጎልተው የወጡና በፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በፌደራል መንግስት የሚመሩለትን የአስተዳደራዊ ወሰን ውዝግቦችን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፤

፭/ ከአስተዳደራዊ ወሰኖች ጋር በተያያዘ የተነሱ ግጭቶች ተፈተው፣ በአጎራባች ክልሎች መካከል ያለው መልካም ግንኙነት የሚታደስበትንና የሚጠናከርበትን መንገድ ያመቻቻል፤

5. <u>Power and Duties Of The Commission</u>

Without prejudice to Powers and Duties that are provided to the House of Federation and Regions under the Constitution and other laws, The Commission shall have the following Powers and Duties:

1/ Provide alternative recommendations to the House of the Federation and the Prime Minister by studying any problems and conflicts that are related to the Administrative Boundaries Demarcation, self-Administration and Issues of Identity;

2/ Provide recommendations to the Prime Minister and the House of the Federation on amendments actions that has to be taken to promote and consolidate unity of Peoples based on equality and their mutual consent;

3/ Provide recommendations, for the continued determination and alteration of Administrative Boundary decisions to; the House of Federation, the House of People's Representatives and the Prime Minister in order to expand appropriate constitutional principles, transparency and efficient system or amendment of laws;

4/ Present recommendations to the House of Federation and The Prime Minister, by investigating Administrative Boundaries controversy which are considerable and directed to it from the House of Federation, The House of People's Representatives and Federal Government;

5/ Facilitate ways in which Conflicts arise over Administrative Boundaries have been resolved, the renewal and strengthen of good relation between neighboring regions;

https://chilot.me

፮/ በቀጣይነት አስተዳደራዊ ወሰኖች የግጭት መንስዔ እንዳይሆኑ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች አስመልክቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤

፯/ አስተዳደራዊ ወሰኖችና አካባቢያቸው አስተማማኝ ሰላም የሰፈነባቸው የልማትና የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሂድባቸው እንዲሆኑ አስተዳደራዊ ወሰኖችን የተመለከተ የፖሊሲ ማዕቀፍ ያመነጫል፤

፰/ የአስተዳደር ወሰን ጉዳዮችን በተመለከት የህዝብ አስተያየት ይሰበስባል፤

፱/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል የስራ ኃላፊዎች፣ የፖለቲካ ቡድኖች፣ እንዲሁም ሌሎች ባላድርሻ አካላት አሰትያየትና ለጥናቱ የሚሆን ግብአት ይሰብስባል፤

፲/ ከህዝብ ግብአትና አስተያየት የሚሰበሰብበትን አካሄድ የሚያሳይ፣ ሂደቱ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ያካተተ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስትራትጂና ዝርዝር እቅድ ያዘጋጃል።

፮. <u>የአስተዳደር ወሰንና የማንነት ጥያቄዎች</u>

ኮሚሽኑ በጥናቱ ግኝት የለያቸው ከራስ በራስ ማስተዳደር፣የአስተዳደር ወሰን እና ከማንነት ጥያቄ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ከሆኑ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል።

፯. <u>የኮሚሽኑ አባላትና አሰያየም</u>

፩/ የኮሚሽኑ አባላት ቁጥር በመንግስት የሚወሰን ይሆናል።

፪/ በኮሚሽኑ አባል ተደርገው የሚሰየሙ ግለሰቦች በሥነ-ምግባራቸው፣ በትምህርት ዝግጅታቸው፣ በስራ ልምዳቸው በማህበረሰቡ የተመሰገኑና መልካም ስም ያተረፉ ይሆናሉ።

6/ Provide recommendations to; The House of The Federation, The House of People's Representatives and the Prime Minister on the measures that has to be taken to make Administrative Boundaries not to be further cause of conflicts;

7/ Initiate policy framework of Administrative Boundaries to make the Administrative Boundaries and their area of well-being for Development and Commerce;

8/ Collect Public opinion on issues of Administrative Boundary;

9/ Collect opinion and inputs for the study from Regional and Federal Officials, Political Parties, and other Stakeholders;

10/ Prepare strategy and detailed plan that show the process of gathering public input and feedback, which ensures that the process includes all sections of the Community.

6. <u>Administrative Boundaries and Identity Issues</u>

The Commission shall Submit issues to the House of Federation, if issues that are identified by the study of the Commission are related to Self-Administration, Administrative Boundary and Identity question.

7. <u>Appointment of the members of the Commission</u>

1/ Number of members of the Commission shall be determined by the government.

2/ Individuals designated as members of the Commission shall have Community commendation and good reputation for their ethical conduct, educational preparation, and work experience.

https://chilot.me

፫/ የኮሚሽኑ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ሌሎች አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሰየማሉ።

3/ The Chairperson of the Commission and the Deputy Chairperson and other members of the Commission shall, up on recommendation by the Prime Minister be appointed by the House of People's Representatives of The Federal Democratic Republic of Ethiopia

፰. የኮሚሽኑ ስብሰባ

8. Meetings of the Commission

፩/ የኮሚሽኑ መደበኛ ስብሰባ በየአስራ አምስት ቀኑ ይካሄዳል፣ ሆኖም እንደየአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡

1/ The Commission shall hold its regular meetings every fifteen days; provided, however that it may hold extraordinary meetings at any time when necessary.

፪/ ከኮሚሽኑ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

2/ There shall be quorum where more than half of the members of The Commission are present at a meeting.

፫/ የኮሚሽኑ ምክረ ሃሳቦች በስምምነት ያልፋሉ፡፡

3/ The Council shall pass its recommendation by consensus.

፬/ በምክረ ሀሳቦች ላይ የጋራ ስምምነት የማይደረስ ከሆነ በአብላጫ ድምፅ ያልፋሉ፡፡

4/ In case of failure to reach consensus on recommendations, decisions shall be made by majority vote.

፭/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሚሽኑ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

5/ without prejudice to the provisions of this Article, The Commission may adopt its own rules on procedure of meeting.

፱. የሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

9. Powers and Duties of the Chairperson of the Commission

የኮሚሽኑ ሰብሳቢ፡-

Chairperson of the Commission shall:

፩/ አጠቃላይ የኮሚሽኑን የስራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፤

1/ Direct the general activities of the Commission;

፪/ ለኮሚሽኑ አስፈላጊ የሆኑ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ይመድባል፤

2/ Assign the necessary supportive staff to the Commission; and

፫/ ኮሚሽኑን በመወከል ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡

3/ Make relation with third parties representing the Commission.

፲. የምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባራት

10. Power and Duties of the Deputy Chairperson of the Commission

የኮሚሽኑ ምክትል ሰብሳቢ፡-

The Deputy Chairperson of the Commission shall:

፩/ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢዉን ተክቶ ይሰራል፡፡

1/ Perform the activity of the chairperson in his absence.

https://chilot.me

፪/ በሰብሳቢው የሚሰጡትን ተግባራት ይፈጽማል።

፲፩. <u>የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት</u>

፩/ የኮሚሽኑ ዋና ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፪/ የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት በመንግስት የሚመደብ የጽህፈት ቤት ኃላፊ ይኖረዋል።

፲፪. <u>የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባራት</u>

የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ለኮሚሽኑ አጠቃላይ የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት ይሰጣል፤

፪/ ለኮሚሽኑ የምርምርና ጥናት አገልግሎት ይሰጣል፤

፫/ ለኮሚሽኑ የህዝብ ተሳትፎና ምክክር መድረኮች የሎጅስቲክስ ድጋፍ ይሰጣል፤

፬/ የኮሚሽኑን ቃለ ጉባኤዎች፣ ውሳኔዎችንና ሰነዶችን አጠናቅሮ ይይዛል፤

፭/ የኮሚሽኑን ስራ ለማሳለጥ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ ያደርጋል።

፲፫. <u>የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ስልጣንና ተግባራት</u>

፩/ የጽህፈት ቤቱን ሰራተኞች እና ሃብት ያስተዳድራል።

፪/ ለኮሚሽኑ አባላት የሚሰጡትን የሴክሪታሪያል እና ሎጅስቲክ ድጋፎች በበላይነት ይመራል።

፫/ የኮሚሽኑን እቅድና በጀት ያዘጋጃል በኮሚሽኑ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።

፬/ ጽህፈት ቤቱን በመወከል ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

2/ perform other activity given to him by the chairperson.

11. <u>Office of the Commission</u>

1/ The head office of Commission shall be in Addis Ababa and may have branch offices on other parts of the country, as may be necessary.

2/ The head of Office of the Commission shall be appointed by the Government.

12. <u>Power and Duties of Office Of The Commission</u>

The Office of The Commission shall have the following Powers and Duties:

1/ Provide general administrative and financial services to the Commission;

2/ Provide research and study services to the Commission;

3/ Provide logistical support to the Commission's public participation and consultation forums;

4/ It shall compile the minutes of the Commission, decisions and documents of the Commission;

5/ Provide the necessary support and assistance to facilitate the work of the Commission.

13. <u>Power and Duties of the Head of the Office</u>

1/ Administer the Office's staff and resource.

2/ Direct the secretarial and logistic support to members of the Commission.

3/ Prepare the work programs and budgets of the Commission and implement same upon approval;

4/ Represent the Office in all dealings with third parties.

https://chilot.me

፲፬. <u>የኮሚሽኑ ገለልተኝነት</u>

ኮሚሽኑ ስራውን በነፃነትና በገለልተኝነት ያከናውናል።

፲፭. <u>የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን</u>

፩/ የኮሚሽኑ አባላት የስራ ዘመን እስከ ፫ ዓመት ነው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም የኮሚሽኑ የስራ ዘመን እንደ ሁኔታው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያራዝመው ይችላል።

፲፮. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ለሚያቀርበው ማንኛውም ህጋዊ እንቅስቃሴ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፲፯. <u>ጠቋሚዎችንና ምስክሮችን ስለመጠበቅ</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ ፊት ቀርቦ በሚሰጠው ቃል መሰረት ክስ ሊመሰረትበት እንዲሁም የሰጠው ቃል በእርሱ ላይ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

፪/ ለጠቋሚዎችና ለምስክሮች ጥበቃ ለማድረግ የወጣ ሕግ ለኮሚሽኑ ቃላቸውን እና መረጃ ለሚሰጡ ሰዎችም ተግባራዊ ይሆናል::

፲፰. <u>በጀት</u>

የኮሚሽኑ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

፲፱. <u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

፩/ የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

14. <u>Neutrality of the Commission</u>

The Commission undertakes the work independently and impartially.

15. <u>Term Of the Commission</u>

1/ The term of Members of the Commission shall be up to 3 years.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article The House of Peoples Representative's may extend term of the Office of Members of the Commission.

16. <u>Duty to Cooperate</u>

Any person shall have an obligation to cooperate with the Commission for any legal questions requested by the Commission while undertaking its responsibility provided under this proclamation.

17. <u>Protection of Witnesses and whistle-blower</u>

1/ No one may be accused by the testimony given to the Commission as well as the testimony given before the Commission could not serve as evidence up on him.

2/ The provisions of the law for the protection of the witnesses and whistle blowers shall apply to those who have provided testimonies and evidences to the Commission.

18. <u>Budget</u>

The Budget of the Commission shall be allocated by the government.

19. <u>Books of Account</u>

1/ The Office Of The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

https://chilot.me

፪/ የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

፳. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳፩. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት

2/ The books of accounts and financial documents of the office shall be audited annually by the Federal General Auditor or by Auditor designated by him.

20. <u>Power to issue Regulation and Directive</u>

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Commission may issue Directives for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

21. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, 8th Day of February 2019,

SAHLEWORK ZEWEDIE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

https://chilot.me

